# ለማጅ ሞያተኛ ማለት ምን ማለት ነዉ?



የተመዘገቡ የለማጅ ሞያ ተከፋይ ሥራዎች ናቸው። በሥራ ላይ በሚሠሩበት ጊዜ ፣ ተለማማጅ ሞያተኞች ከሠለጠነ የዕደ -ጥበብ ባለሙያ እና ከተዛማጅ የክፍል ትምህርት ሥልጠና ያገኛሉ። አንድ ተለማማጅ ሞያተኛ በአሠሪ ወይም በማኅበር ስፖንሰር የሚደረግ እና በደረጃ ክፍያ መሠረት ይከፈላል።

ማሳሰቢያ- የሜሪላንድ የሠራተኛ መምሪያ (The Maryland Department of Labor) ግለሰቦችን ወደ ተለማማጅ መርሐ-ግብር ፕሮግራሞች አያስገባም። ስፖንሰር እና/ወይም ቀጣሪዎች በቀጥታ ሙያተኞችን ይቀጥራሉ።

የጠቅላላው የፊስካል ዓመት 2021 የተለማማጅ ሞያተኛ የሥልጠና መርሃ ግብር በጀት 2,637.107 ዶላር ነው።$ 1,913,356 (73%) በበርካታ የብዙ ዓመታት የአሜሪካ የሠራተኛ መምሪያ (U.S. Department of Labor Grant) በኩል የተደገፈ ነዉ። ሌላዉ $723,751 (27%) ደግሞ ከፌድራል ዉጪ የተደገፈ ነዉ።

# MARYLAND APPRENTICESHIP

## (አማርኛ)



Maryland
DEPARTMENT OF LABOR



# ለእርስዎ ፍጹም የሆነ ሥራ

## ለምን ተለማማጅ ሞያተኛ እሆናለሁ?

ትልቅ ሕልም ለማለም እና ሙሉ እምቅዎን ለማሳካት ዝግጁ ከሆኑ ፣ የተለማማጅ ሙያ ለእርስዎ ትክክል ሊሆን ይችላል።

- እየተማሩ ገንዘብ ያገኛሉ።
- የገቢ አቅምዎን ይጨምራሉ።
- በፍላጎትዎ ላይ ይሆናሉ።
- የኮሌጅ ዕዳን ያስወግዳሉ።
- የባለሙያ ግንኙነቶችን ይገነባሉ።

# ለእርስዎ ፍጹም የሆነ ሥራ

## ለምን ተለማማጅ ሞያተኛን መቅጠር አስፈለገ?

- የሰው ኃይልዎን ይገነባሉ።
- የማዘዋወሪያ ወጪዎችን ይቀንሳሉ።
- ምርታማነትን ያሳድጋሉ።
- ለሠራተኛ ውርስ እቅድ ያወጣሉ።
- የገንዘብ ማበረታቻዎችን ይጠቀማሉ።

## እንዴት ተለማማጅ ሞያተኛ እሆናለሁ?

**ደረጃ** 1 ፦ክፍት የስራ ቦታዎችን ዝርዝር ለማየት occupations.mdapprenticeship.com ን ይጎብኙ።

**ደረጃ** 2፦ከሚገኙ የተላማማጅ እድሎች ጋር ከሚያገናኝዎት የተለማማጅ ሞያተኛ አሳሽ ጋር ለመገናኘት በ (410) 767-2246 ይደውሉ ወይም በ info@mdap-prenticeship.com ኢሜል ይላኩ።

**ደረጃ** 3፦በቀጥታ ለፕሮግራሙ ስፖንሰር ወይም ለቀጣሪው ያመልክቱ።

- ዕድሜዎ 18 ዓመት በላይ ይሁን
- መጓጓዣ ይኑርዎት
- ከአደንዛዥ ዕፅ ነፃ ይሁኑ
- የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዲፕሎማ (በሁለተኛ ደረጃ ምረቃ ፣ ጂ.ኢ.ዲ(GED®) ወይም ኤን.ኢ.ዲፒ (NEDP) አማካይነት) ይኑርዎት
- አስፈላጊ ሥራዎችን ለማከናወን በአካል መገኘት መቻል አለብዎት

## አንድ ተለማማጅ ሞያተኛን እንዴት መቅጠር እችላለሁ?

ደረጃ 1 ፦በ (410) 767-2246 የተለማማጅ ሞያተኛ አሳሽ ላይ ይደውሉ።

ደረጃ 2 ፦የተለማማጅ ሞያተኛ አሳሽ አሁን ካለው የሥልጠና ፕሮግራም ጋር ያገናኝዎታል ወይም የተመዘገበ ተለማማጅ ሞያተኛ መርሃ ግብር እንዲያዳብሩ ይረዳዎታል።

ደረጃ 3 ፦ዕቅድዎን ለሜሪላንድ የተለማማጅ ሞያተኛ እና የሥልጠና ምክር ቤት (the Maryland Apprenticeship and Training Counci) ለማቅረብ እና ለማፅደቅ ከእርስዎ ጋር በጋራ እንሰራለን።

ደረጃ 4 ፦እርስዎ ተለማማጅ ሞያተኞችን መመልመል ይጀምሩ! በእኛ ግዛት የአሜሪካ የሥራ ማዕከላት በኩል ተሰጥኦ ያላቸዉን እንዲያገኙ ልንረዳዎ እንችላለን።.

